# ለታዳግ ልጆች ቤተሰቦች የሚሆኑ አስር ምክሮች

በትናንሽ ልጆችዎ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ በተፈጥሮ ሊካተቱ በሚችሉ፣ በምርምር የተደገፉ እና ቀላል በሆኑ አስር ምክሮች የመማር ሂደታቸውን ይደግፉ። አብሮ ከመነጋገርና ከማንበብ ጀምሮ ጨዋታንና አዳዲስ ነገሮችን ማሰስን እስከማበረታታት ድረስ ያሉት እነዚህ ተግባራዊ ዘዴዎች፤ ለቋንቋ፣ ለንባብና ለጽሕፈት ክህሎት እንዲሁም ለዕድሜ ልክ ትምህርት ጠንካራ መሰረት ለመጣል ያግዛሉ።

በየቀኑ ለልጅዎ ድምፅዎን ከፍ አድርገው ያንብቡ።
- ህጻናት መናገር ከመጀመራቸው በፊትም እንኳ አንብቡላቸው።
- ልጅዎ መጽሐፉን እንዲያይ እና እንዲነካው ያድርጉ።
- በድምፅ እና በቃላት አጠራር ይጫወቱ።

በጽሑፍና በንባብ ቁሳቁሶች የበለጸገ የቤት ድባብ ይፍጠሩ።

- ለልጆች የተለያዩ አይነት መጽሐፍትን ያቅርቡ
- ልጆች መጽሐፍትን በራሳቸው እንዲመለከቱ ያበረታቱ
- ለቤተሰብ ንባብ የሚሆን ቦታ እና ጊዜ ይመድቡ

የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ ግዢን የማንበብ እና የመጻፍ ክህሎትን ለማበረታታት ይጠቀሙበት።
- ልጆችዎ የተወሰኑ ብራንዶችን እንዲያፈላልጉሎት ያድርጉ
- ዕቃዎችን ለማግኘት ከልጅዎ ጋር በመተላለፊያ መንገዶች ላይ ያሉትን ምልክቶች ይጠቀሙ
- ኩፖኖችን ከሚመለከታቸው ምርቶች ጋር ያዛምዱ
- ልጆችዎ የግዢ ዝርዝሮችን እንዲጽፉ ያድርጉ

የንባብ እና የመጻፍ ክህሎትን ለማዳበር ከልጅዎ ጋር ምግብ ያዘጋጁ።
- ልጅዎ የምግብ አዘገጃጀት መመሪያ እንዴት ማንበብ እንዳለበት ያሳዩት።
- በግብዓቶች ላይ ያሉትን መለያዎች አንድ ላይ ያንብቡ።
- ከቤቱ የምግብ አዘገጃጀት መመሪያ ላይ የሚወደደዉን ለቤተሰብ ያዘጋጁ።
- ስለ ቤተሰብ የምግብ አዘገጃጀት መመሪያዎች እና ስለ ምግብ ማብሰያ ምክሮች በመነጋገር የንግግር እውቀትን ያዳብሩ።

ለህፃናት በወረቀት ላይ የታተመዉን ካባብ ያመልክቱ
- በተፈጥሮ ውስጥ በሚደረጉ የእግር ጉዞዎች እና በሌሎችም ውጣ ውረዶች ወቅት የሚታዩ ምልክቶችንና ጽሑፎችን ልብ ይበሉ።ስ
- ለ አርማዎች (logos) ይወያዩ።
- ልጆች ከቤት ውጭ የሚታዩ ጽሑፎችን እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው።

አብራችሁ ታሪኮችን ተረኩ
- ስለ ቤተሰብዎ ታሪክ አብረው ይወያዩ
- የድሮ የእረፍት ጊዜ ፎቶዎችን ይመልከቱ እና ስለ ጉዞው ያለዎትን ትዝታ ያውሩ
- ታሪኮችን ሲያወሩ ድምፅዎን ወይም ምስልዎን ይቅረጹ
- የቤተሰብ ፎቶ አልበሞችን ያዘጋጁ እና ለፎቶዎቹ መግለጫዎችን በመጻፍ ረገድ ልጅዎ እንዲያግዝዎ ያድርጉ



©2026 Reading Is Fundamental

# ለታዳጊ ልጆች ቤተሰቦች የሚሆኑ አስር ምክሮች

Reading Is Fundamental. until every child reads

ከልጅዎ ጋር ዘምሩና ግጥም ተጫወቱ።
- በግጥም መልክ የሚሄዱ (ሪዝም ያላቸው) እና በቃላት አጨዋወት የተሞሉ ዘፈኖችን ይምረጡ።
- ከልጅዎ ጋር እንደ “ከ‘honey’ (ማር) ጋር ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸው ሌሎች ቃላት የትኞቹ ናቸው?” ያሉ የቃላት ጨዋታዎችን ይጫወቱ።
- ልጅዎ ግጥሞችን በተቻለ ፍጥነት እንዲዘፍን ወይም እንዲናገር ያበረታቱት፤ ውጤቱ አስቂኝ ከሆነም አብረው መሳቅዎን አይዘንጉ።

ከልጅዎ ጋር ይጻፉ
- በርካታ የመጻፊያ ቁሳቁሶችን ያቅርቡ(ኖራ፣ ማርከር፣ ክሬዮን እና እርሳስ) ።
- ልጅዎ በራሱ ተነሳሽነት እንዲስልሉእና እንዲጽፍፉ ያበረታቱ።
- ልጅዎ ለአያቶቹ የምስጋና መልዕክቶችን እንዲጽፍ፣ የሚከናወኑ ተግባራት ዝርዝር እንዲያዘጋጁ እና የመሳሰሉትን እንዲያደርጉ ያበረታቱ።

ማንበብና መጻፍን ከሥነ ጥበብ ጋር ማያያዝ
- አብራችሁ የሥነ-ጥበብ ሙዚየምን ጎብኙ፤ በሥነ-ጥበብ ሥራው ውስጥ ምን እየተከናወነ እንዳለ ለማስረዳትም ታሪክ የመተረክ ዘዴን ተጠቀሙ። ልጅዎ የሥነ-ጥበብ ሥራውን በራሳቸዉ እይታ እንዲተረጉሙ እድል ስጡአቸዉ።
- ልጆች የራሳቸውን ስዕሎች፣ ቅርጻ ቅርጾች፣ እንዲሁም እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ ከሚችሉ ቁሶች የሚሠሩ የጥበብ ሥራዎችን በመኖሪያ ክፍላችሁ ውስጥ እንዲፈጥሩ ያድርጉ።
- ልጆች ስለ ሥራቸው የሚናገሩትን ሐሳብ በአረፍተ-ነገር መልክ በወረቀት ላይ በመጻፍ የጥበብ ሥራውን ያስረዱ (ልጆች ስለ ሥራቸው ታሪክ የሚተርኩበትን ድምፅ የመቅረጽ አማራጭንም ያስቡበት)።

ቤተ መፃህፍትን (እና/ወይም የመጻሕፍት መደብርን) ብዙ ጊዜ ይጎብኙ
- በተቻለ መጠን በተደጋጋሚ ጉብኝቶችን ያድርጉ።
- ልጅዎ የራሳቸዉን የቤተ-መጻሕፍት ካርድ እንዲያወጡ ያበረታቱ።እንደ ጮክ ብሎ የማንበብ ክፍለ-ጊዜዎች እና የቤተሰብ የመጽሐፍ ክለቦች ያሉ የቤተ-መጻሕፍት ፕሮግራሞችን ይጠቀሙ።

*ይህ የምክር ጽሑፍ በሌሎች ቋንቋዎችም ይገኛል። በ rif.org ላይ ያገኟቸዋል።.



©2026 Reading Is Fundamental

Reading Is Fundamental.